አፍሪካ ቲቪ

3

# ሁሉም ሙስሊም ማወቅ ያለበት “የልብ ተግባራት”

በቴሌግራም

3

አፍሪካ አካዳሚ

AFRICA ACADEMY

AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

## ከልብ ተግባራት መካከል የተወሰኑት ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ናቸው፡፡

- **እነርሱም፡- ኒያ /ማሰብ/፤** መመኘት፤ መፈለግ ማለት ሲሆን፡፡ የትኛውም ተግባር ያለ ኒያ ብቃት ተቀባይነትም የለውም፡፡
- ነብዩ ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲሰ ‹‹ተግባራት ሁሉ ያለ ኒያ ብቃት የላቸውም፡፡ ሰዎች የሚመነዱት እንደንያቸው ነው›› ብለዋል፡፡
- ኢብኑ ሙባረክ (በኒያ የተነሳ ከፍተኛ ደረጃ የሚደርሱ አነስተኛ ተግባራት እንዳሉ ሁሉ እንደዚሁም በኒያ የተነሳ ዋጋ የሚያጡ አያሌ ተግባራት አሉ) ብለዋል፡፡
- ፉዶይል ኢብኑ ኢያድ ‹‹ አላህ ከአንተ የሚፈልገው ኒያህን ነው፡፡ እናም ኒያህ ለአላህ ከሆነ ኢኺላስ ይባላል፡፡ ከዚህ ሌላ ከሆነ ግን የዩልኝ፤ ንፍቅና ሌላ ሌላም ይባላል›› ብለዋል



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

## ጠቃሚ ምክር

- ዓሊሞች ሲቀሩ ሰዎች ሁሉም ጠፍተዋል፡፡
- ተግባሪዎች ሲቀሩ ዓሊሞች ሁሉ ጠፍተዋል፡፡
- ፍፁማውያን (ከልባቸው በኢኽላስ የሚሰሩ) ሲቀሩ ተግባሪዎች ሁሉም ጠፍተዋል፡፡
- ስለዚህ አላህን ለመገዛት ለፈለገ ሰው ሁሉ የመጀመሪያው ተግባር ኒያን መማር ነው፡፡ ከዚያም ፍፁምነትን በትክክል በመረዳትና በማወቅ ኒያን ማስተካከል ነው፡፡
  ያለ ኒያ ተግባር አጉል ልፋት ነው፡፡ ያለፍፁምነት ኒያ ማድረግም ይዉልኝ ነው፡፡ እምነት ሳይኖር ፍፁምነት ደግሞ ዋጋ ቢስ ነው፡፡



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

አፍሪካ ዲናዊ እውቀት አካዳሚ

(ሁሉም ሙስሊም ማወቅ ያለበት "የልብ ተግባራት")

አፍሪካ አካዳሚ

## ተግባራት ሶስት አይነት ናቸው፡፡

1) **ወንጀሎች ናቸው፡፡** እናም ኒያ ወንጀልን ወደ መልካም አምልኮ ተግባርነት አይቀይርም፡፡ ከቶውንም መጥፎ ኒያ ከተጨመረበት ቅጣቱ እጥፍ ድርብ ይሆናል፡፡

2) **የተፈቀዱ ነገሮች ናቸው፡፡** የትኛውም የተፈቀደ ተግባር አንድ አይነት ወይም የተለያየ ኒያ ሊኖረው ይችላል፡፡

እናም ከታሰበበት ወደ ዒባዳ ሊቀየር ይችላል ማለት ነው፡፡

3) **አምልኮቶች ናቸው (ጣዓ)፡፡**

እነዚህ ተግባራት ለብቃታቸውም ሆነ አጅራቸውን ለማብዛት ኒያ የግድ ያስፈልጋቸዋል፡፡

- አንድ ሰው በተግባሩ ለዩልኝ ካሰበ ተግባሩ ወንጀል ይሆንበታል፡፡
- ብሎም ወደ መለስተኛ ሺርክነት ደረጃም ይደርሳል፡፡
- እንደ ሁኔታው ከዚያም አልፎ ወደ ከፍተኛ ሺርክ ሊያድግ ይችላል፡፡

3

- እሱም በሶስት ይከፈላል፡፡

1. በመጀመሪያ ለሰው ብሎ መስራት ሲሆን ይህ ተግባር ሺርክ ነው፡፡

   በዚህ እሳቤ የፈፀመው ኢባዳውም ባጢል ነው፡፡

2. ተግባሩ ለአላህ ሆኖ የዩልኝ ስሜቱ ኋላ የመጣበት ከሆኑ የተግባሩ መጨረሻ በመጀመሪያው ላይ ያልተመሰረተ ከሆነ ለምሳሌ ሰደቃን ይመስል መጀመሪያው ልክ ነው (ተቀባይነት ይኖረዋል) በመጨረሻው ግን ባጢል (የተበላሸ) ነው፡፡

   የተግባሩ መጨረሻው ከመነሻው ጋር የተያያዘ ከሆነ በሁለት መልክ ይታያል፡፡

- ሀ. የዩልኝን ከተከላከለ በተግባሩ ላይ ምንም ተፅዕኖ አያደርግበትም፡፡
- ለ. ይዩልኝን በደስታ ተቀብሎ የሚያስተናግድ ከሆነ ግን ተግባሩ ዋጋ ቢስ ውድቅ ነው፡፡



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

3. ልታይ ባይነቱ ከተግባሩ በኋላ የተከሰተ ከሆነ ይህ አይነቱ ኒያ ምንም አይነት ተፅዕኖ አያሳድርም በተግባሩም ላይ በተገበረው ላይ እዚህ ላይ ብዙ ልታይ ባይነትን የሚመለከቱ ጉዳዮች አሉና ሁሉም ሙስሊም አውቋቸው ሊጠነቀቃቸው ይገባል፡፡

- መልካም ስራውን ሲፈፅም ያሰበው የዚህች ዓለምን ደስታ ለማግኘት ብቻ ከሆነ ምንዳውም ሆነ ቅጣቱ በኒያው ልክ ነው፡፡

- መልካም ስራውን ሲፈፅም ያሰበው የዚህች ዓለምን ደስታ ለማግኘት ብቻ ከሆነ ምንዳውም ሆነ ቅጣቱ በኒያው ልክ ነው፡፡ ***እሱም በሶስት ይከፈላል፡፡***

- **1)** ለዚህ ተግባር ያነሳሳው ዱንያዊ እሳቤ ብቻ የሆነ ሲሆን ይኸውም ለገንዘብ ብቻ ብሎ ሶላት እንደሚያሰግድ ሰው ሲሆን ይህ ሰው ምንም አይነት ምንዳ የሌለው ወንጀል ብቻ ነው የሚያከማቸው፡፡

- ነቢዩ ሰ.ዐ.ወ አቡዳውድ በዘገቡት ሐዲስ ‹‹የአላህ ፊት ከሚፈለጉበት ትምህርቶች ውስጥ የዱንያን ጥቅም ብቻ እሳቤ አድርጎ የተማረ ሰው የቂያማ ዕለት የጀነትን ሽታ እንኳን አያገኝም፡፡ ››

- **2)** ለአላህና ለዱንያ ለጥቅም ብሎ የሰራ ሰው እምነቱም ሆነ ኢኽላሱ የጎደለ ሰው ነው፡፡ የዚህም ምሳሌው ሐጅን ሲተገብር ንግድ አብሮ የነየተ ሰው ነው፡፡ የዚህ ሰውየ ምንዳው በኢኽላሱ ልክ ነው፡፡



AAcademyEthio
www.AfricaAcademy.com

3) ለአላህ ብቻ ብሎ ሰርቶ ለኑሮው የሚሆን ክፍያ የሚቀበል ሲሆን ይህ አይነቱ በተቀበለበት ደመወዝ ምክንያት በአኼራ ከሚያገኘው ምንም አይጎልበትም፡፡

- ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ ‹‹ክፍያ ከተቀበላችሁባቸው ነገሮች ሁሉ ዋናው የአላህ መፅሐፍ (ቁርኣን) ነው፡፡›› ብለዋል፡፡

- **ተግባራቸውን በፍፁምነት የሚያሰሩ ሰዎች የተለያዩ ደረጃዎች አሏቸው፡፡**

**1)** ዝቅተኛው ሲሆን ይኸውም ተግባሩን የሚፈፅመው ምንዳ ለማግኘትና ከቅጣት ነፃ ለማውጣት ብሎ የሚተገብር ነው፡፡

**2)** መካከለኛው ነው አላህን ለማመስገንና ተዕዛዙን ለማክበር ብሎ የሚፈፅመው ነው፡፡

**3)** ከፍተኛው ሲሆን እሱም ተግባሩን ለአላህ ውዴታና ክብር ብሎ የሚሰራ ሲሆን ይህ የሲዲቆች፤ ደረጃ ነው፡፡

3